# የምዝገባና የአስተያየት ቅጽ

ለመመዝገብና አስተያየት ለመስጠት እባክዎ ሳሙዔል ሀይሉን ወይም ኖምሳን ያነጋግሩ


ሳሙዔል ሃይሉ ቲ.ኤስ ኢንቫይሮሜንታል ቴክኖሎጂ
ስልክ፡- +251911373167 ኢሜይል፡- sam1hy@yahoo.com

ኖምሳ Fulbrook-Bhembe: ኢንቫይሮሜንታል ሪሶርስስ ማኔጅመንት
ስልክ፡- +447824825250 ኢሜይል፡- Nomsa.fulbrook-bhembe@erm.com

ያራ ዳሎል ቢቪ 3ኛ ፎቅ፣ አሲስ ህንፃ፣ ከኢድናሞል አጠገብ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ፡- +251 (0) 9141 524 489 ፋክስ፡- +251 11 6630967


በተጨማሪም ሰለ ኢ.ኤስ.አይ.ኤ ተጨማሪ መረጃ ከኢ.ኤስ.አይ.ኤ ፕሮጀክት ደረ-ገጽ ይመልከቱ፡-
http://www.erm.com/Yara-Dallol-BV-Potash-Project-EIA.

| | | | |
|---|---|---|---|
| እባክዎ እንደ እንድ የሚመለከተው አካል ይመዝግቡኝና ተጨማሪ መረጃዎች ይድረሱኝ | | አዎ | አይ |
| ማስታዎቂያዎች እንዲደርሱኝ የምፈልገው በ፡- | ኢሜይል | ፖስታ | ፋክስ |

አስተያየቶች

የሚገኙበት ዝርዝር መረጃ ወደ ፕሮጀክቱ የመረጃ ቋት ይገባ ዘንድ የሚከተሉትን ይሙሉ፡-

| | |
|---|---|
| ማዕረግ እና ስም | |
| ድርጅት | |
| ስልክ | ተንቀሳቃሽ ስልክ |
| የፖስታ አድራሻ፡- | ፋክስ፡- |
| ኢሜይል፡- | |

## ስለተሳተፉ እናመሰግናለን

# ያራ ዳሎል ፖታሽ ፕሮጀክት

## የኋላ ታሪክ መረጃ ሰነድ

## የዚህ ሰነድ ተግባር

የዚህ ሰነድ ተግባር ስለታቀደው የያራ ዳሎል ፖታሽ ፕሮጀክት (ስለታቀደው ፕሮጀክት) እና አሁን እየተካሄደ ባለው የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ ዳሰሳ (የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት) ላይ የሚመለከታቸው አካላት ተሳታፊ ስለሚሆኑበት አካሄድ አጭር ማብራሪያ ለእርስዎ መስጠት ነው። የላቀ ተጠቃሚነት ይኖር ዘንድ የሚመለከታቸው አካላት መረጃ እንዲያገኙና ስጋቶቻቸውንና አስተያየቶቻቸውን እንዲያቀርቡ እድል ለመስጠት፣ በኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት ልዩ ልዩ ደረጃዎች ተጨማሪ ሰነዶች የሚኖሩ ይሆናል።





## መግቢያ

ያራ ኢንተርናሽናል (ያራ) የግብርናና የማዳበሪያ ምርቶችን (እንደ ፖታሽ አይነት) ጨምሮ የአካባቢ ኤጀንቶችን በማምረት የታወቀ የኬሚካል ኩባንያ ነው። ይህን ለመደገፍ፣ በኢትዮጵያ የደናክል ረባዳማ ቦታ የፖታሽ ማዕድን ለመፈለግና ለማልማት የሚሰራ ያራ ዳሎል ቢቪ የተባለ ንዑስ ኩባንያ በያራ ተመስርቶል። ያራ ዳሎል ቢቪ ቀደም ሲል በተጠቀሰው መሰረት የፖታሽ ማዕድን የሚያመርት ክፍል ለመመስረት የፕሮጀክት ቀረጻና ማኔጅመንት ስራ ከሚሰራውና ኖቮፕሮ ፕሮጀክትስ ኢንኮርፖሬትድ (ኖቮፕሮ) ከተባለው የካናዳ ኩባንያ ጋር በጋራ ይሰራል። ያራ «ሶሉሽን ማይኒንግ» ተብሎ በሚጠራ ሂደት ፖታሽ ለማውጣት ሀሳቡን ያቀርባል («ሶሉሽን ማይኒንግ» ሂደትን በተመለከተ ገጽ 2 ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ)።

የታቀደው ፕሮጀክት በአፋር ክልል በደናክል ረባዳማ ቦታ (ዞን 2፣ ዳሎል ወረዳ) ይገኛል። የታቀደው ፕሮጀክት አጠቃላይ ስፋት 64 ኪ.ሜ2 ነው።

የታቀደው ፕሮጀክት ከ3 አመታት በላይ ያሳለፈ ሲሆን በተለያዩ ስያሜዎች ለምሳሌ ሴይኒክ ኮል ማይኒንግ ፒ.ኤል.ሲ፣ ሴይኒክ ፖታሽ ፒ.ኤል፣ ኢትዮፖታሽ ቢቪ እና ያራ ዳሎል ቢቪ ፕሮጀክት በመሳሰሉት ስያሜዎች ሲጠቀም ቆይቷል። የታቀደው ፕሮጀክት የተለያዩ ስያሜዎችን ሲጠቀም የቆየበት ምክንያት የማዕድን ማውጣቱ ስምምነት ባለቤት ስለተቀያየረ ነው።








## የሶሉሽን ማይኒንግ ሂደት

1




ወደ 200ሜ የሚጠጋ ጉድጓድ ከመሬት ውስጥ መቆፈርና ወደ ውስጥ ውሃ በመልቀቅ የፖታሽ ክምችቱ እንዲሟሟ ማድረግ።

2

በመሬት ውስጥ የሚሟውን ጨዋማ የፖታሽ ቅልቅል ፈሳሽ የያዙ ትልልቅ ዋሻዎች ይፈጠራሉ። ይህ ፈሳሽም ወደ መሬት ገጽ ይወጣል።

3

ቅልቅሉ ፈሳሽ በቱቦዎች ውስጥ ወደ ማትነኛ ኩሬዎች ይጓጓዛል።



በፀሀይ ትነት

4

ይህ ቅልቅል ፈሳሽ በማትነኛ ኩሬዎች ውስጥ ይደርቅና ጠጣር ፖታሽ ይቀራል።

ድፍድፍ ፖታሹን ትራክተር ይሰበስበውና ወደ ማቀነባበሪያ ፋብሪካው ያስተላልፈዋል።



5

ፖታሹን ከቆሻሻው በመለየት ከፍተኛ ጥራት ያለው የፖታሽ ምርጽ ለማምረት ማቀነባበር።



6

የፖታሹ ምርት ወደ ጂቡቲው የታጁራ ወደብ ይተላለፋል



## ከታቀደው ፕሮጀክት ጋር ተያያዥ የሆኑ መሰረተ ልማቶች



ማሽንና መሳሪያዎች



ማቀነባበሪያ ፋብሪካ



ነዳጅ



መግቢያና መስብሰቢያ መንገዶች



የኤሌክትሪክ ሀይል መስመር



ማትነኛ ኩሬዎች



የግንባታና የስራ ማስኬጃ ካምፕ




ተሽከርካሪዎች



ከላይ ከተጠቀሱት ተያያዥ መሰረተ ልማቶች በተጨማሪ፣ የሶሉሽን ማይኒንግ ሂደቱን ለመስራትና አጠቃላይ የታቀደውን ፕሮጀክት ለማከናዎን የሚያስፈልጉ እንደ መሬትና ወሃ አይነት ሌሎች ግብዓቶችም ለያራ ዳሎል ቢቪ አስፈላጊ ግብዓቶች ናቸው።

የታቀደውን ፕሮጀክት ለማከናወን ሰራተኞችም ያስፈልጋሉ። በግንባታውና በስራው ክንውን ወቅት ክህሎት ያላቸውንና የሌላቸውን ሰዎች የሚያካትት 370 እና 580 ያህል ሰራተኞች እንደሚያስፈልጉ ይጠበቃል። በተቻለ መጠን በአካባቢውና በአፋር ክልል ውስጥ በሚገኙ ሌሎች አካባቢዎች የሚኖሩ ሰራተኞችን ለመቅጠር ያራ ዳሎል ቢቪ ጥረት ያደርጋል።

ኢ.ኤስ.አይ.ኤ የታቀደው ፕሮጀክት ሊያመጣቸው የሚችላቸውን ዋና ዋና ለውጦች (ተጽዕኖዎች) የሚለይ ይሆናል።

የታቀደው ፕሮጀክት በተፈጥሮአዊው አካባቢና በሰዎች ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ሊመጡ የሚችሉት የተወሰኑ ተጽዕኖዎች ከዚህ በታች ተመልክተዋል። ተጽዕኖዎቹ በኢ.ኤስ.አይ.ኤ የመነሻ ጥናትና የተጽዕኖ ዳሰሳ የጥናት ክፍሎች በበለጠ ጥልቀት የሚጠኑና ግንዛቤ የሚወሰድባቸው ይሆናል። እነዚህን የተጽዕኖ አይነቶች ለማስወገድ እና/ወይም ለመቀነስ በተጽዕኖ ዳሰሳ የጥናት ክፍል የጉዳት መቀነሻ ርምጃዎች ይዘጋጃሉ። በተጨማሪም ማንኛውንም አወንታዊ ተጽዕኖዎች ለመደገፍ የሚረዱ ጥቆማዎች ይዘጋጃሉ።



የአየር ልቀት ችግር



የጸጥታ መታወክ ችግር



የውሃ ሀብት መጠቀም



የአካባቢ ነዋሪዎች የመታወክ ችግር



አካባቢው የመረበሽና የመጎዳት ችግር



የህዝብ ብዛት የመጨመር ችግር



የትራፊክ አደጋዎች የመጨመር ችግር



ዝቅተኛ የሆነ የሰራተኛ ደረጃዎች ችግር



የአካባቢው እይታ የመቀየር ችግር



የባህላዊ ቅርሶችና የአርኪዮሎጂ መረበሽ ችግር



የአካባቢዎች የመጓጓዣ መንገዶች የመቋረጥ ችግር



የተሻለ ገቢ የማግኘት አጋጣሚዎች (ከስራ ቅጥርና ከሸቀጦችና ከአገልግሎቶች ግዢ)

## ተጽዕኖዎችን ማስተናገድ

በርካታ መነሻ ጥናቶች የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት አካል ሆነው የሚከናወኑ ይሆናል። መነሻ ጥናቱና ተያያዥ የተጽዕኖ ዳሰሳ ጥናቶች አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስና አወንታዊ ተጽዕኖዎችን ለመደገፍ የሚያችሉ መንገዶችን የሚጠቁሙ ይሆናል።

ይህም የሚከናወነው አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያገለግል የጉዳት መቀነሻ ርምጃ በመቅረጽ ነው። የታቀደው ፕሮጀክት የሚኖረውን አወንታዊ ተጽዕኖ ለማገዝ ጥቆማዎች የሚዘጋጁ ይሆናል።



የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደቱ የሚከናወነው በኢትዮጵያ የ1997 የአካባቢ ፖሊሲና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/2002 መሰረት ነው። ኢ.ኤስ.አይ.ኤ በሚከተሉት አምስት ቁልፍ ክፍሎች የተከፈለ ነው፡- መለየት፣ ስኮፒንግ፣ የመነሻ ዳታ መሰብሰብ፣ የተጽዕኖ ዳሰሳና ይፋ ማድረግ፤ ከታች ይመልከቱ።

በኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት በሙሉ የሚመለከታቸውን አካላት የማሳተፍ ተግባር ይሰራል።

መለየት የመጀመሪያው ተግባር ነው። በኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት ምን ምን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ እንደሚገቡ ይወሰናል።

ይፋ በማድረጉ ሂደት ኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሪፖርት በመንግስት እንዲገመገምና ውሳኔ እንዲሰጥበት ይቀርባል።

የተጽዕኖ ዳሰሳው የታቀደው ፕሮጀክት በአካባቢውና በአካባቢው በሚኖሩ ሰዎች ላይ የሚያስከትላቸውን አወንታዊም ሆኑ አሉታዊ ተጽዕዎች፣ ስለሚኖሩት ለውጦች (ተጽዕኖዎች) ደረጃ፣ እንዲሁም እነዚህን ተጽዕኖዎች እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል ያጠናል፣ ይተነትናል።.




ስኮፒንግ (Scoping) በታቀደው ፕሮጀክት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ለውጦችን (ተጽዕኖዎችን) ይለያል።

**አሁን የምንገኘው በስኮፒንግ ደረጃ ነው።**

የመነሻ ዳታ መሰብሰብ የታቀደው ፕሮጀክት ከመጀመሩ በፊት ስለአካባቢውና በአካባቢው ስለሚኖሩ ሰዎች መረጃ ለመሰብሰብ የሚሰራ ስራ ነው።

## የሚመለከታቸውን አካላት ማሳተፍ

የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት ወሳኙ ክፍል የታቀደው ፕሮጀክት ከሚነካቸው ወይም በፕሮጀክቱ ዙሪያ ፍላጎት ከአላቸው ሰዎች ጋር መነጋገር ነው። ይህም የሚመለከታቸውን አካላት ማሳተፍ የሚባል ሲሆን በኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት በሙሉ ይከናወናል። የሚቻል እስከሆነ ድረስ የታቀደውን ፕሮጀክት ለማሻሻል የሚመለከታቸው አካላት ያላቸው እይታ ከግምት ውስጥ ይገባል።

ኢ.አር.ኤም እና ቲ.ኤስ ኢንቫይሮሜንታል ቴክኖሎጂ የተባሉት ድርጅቶች የሚመለከታቸውን አካላት የማሳተፉን ሂደት የሚያከናውኑ ገለልተኛ አማካሪዎች ናቸው። የሚመለከታቸውን አካላት የማሳተፉ ሂደት ለሁሉም አካላት በተለይም ደግሞ የታቀደው ፕሮጀክት ለሚነካቸው አካላት ክፍት መሆኑን ለማረጋገጥ የእኛ ቡድን ጥረት ያደርጋል። ይህም የሚከናወነው ለባህል በሚስማማ መልኩ ነው።

## እርስዎ እንዴት መሳተፍ ይችላሉ?

ማንኛውም ጥያቄ ወይም ስጋት ከአለዎትና እንደ ባለድርሻ አካል ለመመዝገብ የሚፈልጉ ቢሆን፣ በሚከተሉት አማራጮች መሳተፍ ይችላሉ፡-

- በኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት በሚካሄዱ ወርክሾፖችና ህዝባዊ ስብሰባዎች መሳተፍ፤
- የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ፕሮጀክቱን ድረ-ገጽ መጎብኘት (http://www.erm.com/Yara-Dallol-BV-Potash-Project-EIA.)
- ለተጨማሪ መረጃ ኢ.አር.ኤም እና ቲ.ኤስ ኢንቫይሮሜንታል ቴክኖሎጂን ማነጋገር (የሚገኙበትን አድራሻ ዝርዝር ገጽ 6 ይመልከቱ)፤ እና
- በታቀደው ፕሮጀክት እንደ አንድ የሚመለከተው አካል ወይም ፍላጎት ያለው አካል መመዝገብ። መመዝገብ ስለ ኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደትና ስለታቀደው ፕሮጀክት ተጨማሪ መረጃዎች እንዲደርሱዎት ያችልዎታል።







## የፕሮጀክቱ ደረጃዎች

የታቀደው ፕሮጀክት ለ3 አመታት ያህል በማልማት ደረጃ ላይ ቆይቷል። የታቀደው ፕሮጀክት የማልማት ደረጃ ሴስሚክ ጥናትን፣ኮር ድሪሊንግና የመጀመሪያ ደረጃ የአካባቢና ማህበራዊ ጥናቶችን ማጠናቀቅን ያካተተ ነበር።

በአሁኑ ጊዜ የታቀደው ፕሮጀክት በአዋጭነት ጥናት ደረጃ ላይ ይገኛል። የአዋጭነት ጥናቱም የሙከራ ማዕድን ማውጣትንና የአካባቢያዊና የማህበራዊ ተጽዕኖ ዳሰሳ (ኢ.ኤስ.አይ.ኤ) ጥናቱን ማጠናቀቅን፣ እንዲሁም የታቀደውን ፕሮጀክት አዋጭነት በተመለከተ ሌሎች ጥናቶችን ማድረግን ያካትታል።

የአዋጭነት ጥናቶች የታቀደው ፕሮጀክት አዋጭ እንደሆነ የሚያሳዩ ከሆነ፣ የታቀደው ፕሮጀክት ወደ ዝርዝር የምህንድስና ስራዎች ደረጃዎች ይሸጋገራል። ወደ ግንባታ ስራው ደረጃ ከመገባቱ በፊት በዝርዝር የምህንድስና ስራዎች ደረጃ የታቀደው ፕሮጀክት ዲዛይን ይጠናቀቃል።

የታቀደው ፕሮጀክት እ.ኤ.አ በ2017 መጨረሻ ላይ የመጀመሪያውን የፖታሽ ምርት የማምረት ተግባሩን እንደሚጀምር ይጠበቃል። የማዕድን ማውጣቱ የቆይታ እድሜ 18 ዓመታት እንደሚሆን ይታሰባል።

የአዋጭነት ጥናቶች — ምህንድስናና ግንባታ

2010 — 2013 — 2014 — 2015 — 2016 — 2017 — 2018

2010: የማልማት ደረጃ— ቁፋሮ፣ የአሰሳ ቁፋሮ፣ የሃይድሮሎጂካል ጥናቶች፣ ወዘተ።

2015: ኢ.ኤስ.አይ.ኤ

2018 →: ትግበራዎች

## ኢ.ኤስ.አይ.ኤ ለምን?

ያራ ዳሎል ቢቪ በስራው ከመግፋቱ በፊት፣ የታቀደው ፕሮጀክት በዙሪያው በሚገኙ ተፈጥሮአዊ አካባቢዎችና በነዋሪዎች ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ በተመለከተ የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደትን በመጠቀም ጥናት ማድረግ አለበት።

## ኢ.ኤስ.አይ.ኤ ምንድን ነው?

የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ ዳሰሳ (ከእንግሊዝኛው ምህጻረ ቃል ኢ.ኤስ.አይ.ኤ) በማከናወን የታቀደው ፕሮጀክት አሁን ያለውን አካባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታ በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ እንዴት ሊቀይረው እንደሚችል ለመረዳት ጥናት በመደረግ ላይ ነው።

በተጨማሪም፣ የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሂደት በታቀደው ፕሮጀክት አማካኝነት የሚከሰቱ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስና የሚፈጠሩ ተጠቃሚነቶችን (አወንታዊ ተጽዕኖዎችን) ለማሳደግ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይለያል።

16. የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሪፖርት የታቀደው ፕሮጀክት ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መልማት የሚችል ስለመሆኑንና እንዴትስ መልማት እንደሚችል ምክር ይሰጣል እንዲሁም የኢትዮጵያ ባለስልጣናትን ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ያግዛል።

## የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ዳሰሳ የሚያካሂደው ማን ነው?

በኢትዮጵያ የ1997 የአካባቢ ፖሊሲና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/2002 መሰረት ያራ ዳሎል ቢቪ የኢ.ኤስ.አይ.ኤ ሪፖርት ለኢትዮጵያ መንግስት በማቅረብ እንዲታይ ማድረግ ይጠበቅበታል። ኢንቫይሮሜንታል ሪሶርስስ ማኔጅመንት (ኢ.አር.ኤም) ገለልተኛ አማካሪ ድርጅት ሲሆን የታቀደውን ፕሮጀክት ኢ.ኤስ.አይ.ኤ ከኢትዮጵያዊ አማካሪዎች ቲ.ኤስ ኢንቫይሮሜንታል ቴክኖሎጂና ከኢ.ኤስ.ኤስ.ዲ እንደ ቅደም ተከተላቸው የማህበራዊና አካባቢያዊ አማካሪዎች ጋር በመሆን እያከናወነው ይገኛል።







ኢ.ኤስ.አይ.ኤ አምስት ቁልፍ ጥያቄዎችን የመመለስ ዓላማ አለው

**መነሻ**

**1** — አሁን ያለው አካባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ምን ይመስላል

**ትንበያ**

**2** — የታቀደው ፕሮጀክት የሚያስከትላቸው ተጽዕኖዎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ? በታቀደው ፕሮጀክት አማካኝነት በአካባቢውና በማህበረሰቡ ውስጥ ሁኔታዎች እንዴት ይቀየራሉ?

**ግምገማ**

**3** — ተጽዕኖዎቹ ክብደት የሚሰጣቸው ናቸው? ከሆነ፣ ምን ያህል ክብደት አላቸው?

**ጉዳት መቀነስ**

**4** — ተጽዕኖው ክብደት የሚሰጠው ከሆነ፣ ጉዳቱን ለመቀነስ፣ ለማስተካከል ወይም ለማካካስ ምን ማድረግ ይቻላል? ወይም ጥቅሞችን ማሳደግ?

**ቀሪ ተጽዕኖዎች**

**5** — የጉዳት መቀነስ ርምጃ ከተወሰደ በኋላ የሚቀሩት ተጽዕኖዎች ምንድን ናቸው? እነዚህስ ምን ያህል ክብደት የሚሰጣቸው ናቸው?

